የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.36
ADDIS ABABA, 23rd March , 2018



**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፫/፪ሺ፲ ዓ.ም

ህገመንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ ማፅደቂያ አዋጅ ......................................... ገፅ ፲ሺ፫፻፴፩

**CONTENT**

Proclamation No.1083/2018

Constitution and Constitutional order Defence from Threat State of Emergency Proclamation No.2/2018 Approval Proclamation ……………………..page 10331


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፫/፪ሺ፲

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ህገ መንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ህገመንግስቱን እና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የሚኒስትሮች ምክር ቤት የካቲት ፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጀ በመሆኑ፣

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሕገመንግስቱ አንቀፅ ፺፫(፪)(ለ) መሰረት በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ ያለበት በመሆኑ፣

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀፅ ፺፫ (፪) (ለ) እና አንቀፅ ፶፭ (፰) መሰረት የሚከተለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጇል::

## PROCLAMATION No.1083/2018

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE CONSTITUTION AND CONSTITUTIONAL ORDER DEFENCE FROM THREAT STATE OF EMERGENCY ETHIOPIAN FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC COUNCIL OF MINISTERS PROCLAMATION**

**WHEREAS**, the Council of Ministers has approved on 16th day of February 2018 the Constitution and Constitutional order Defence from Threat State of Emergency Proclamation;

**WHEREAS,** based on Article 93 (2) (b) of the Constitution, the State of Emergency Proclamation decreed by the Council of Ministers shall be presented to the House of Peoples' Representatives within fifteen days;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives has ratified this proclamation on the 2nd day of March 2018;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 93 (2) (b) and Article 55 (8) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, the State of Emergency Proclamtion is hereby proclaimed as follows:

**፩.<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ህገመንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር "፩ሺ፹፫/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. <u>የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ስለማፅደቅ</u>**

የካቲት ፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ህገመንግስቱን እና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቋል።

**፫.<u>አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ</u>**

፩/ ህገመንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ከአደጋ ለመከላከል በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ የተመለከተው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀፅ ፺፫ (፭) እና (፮) እና በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፪/፪ሺ፲ አንቀፅ ፰ እና አንቀፅ ፱ በተመለከተው መሰረት ስልጣንና ሀላፊነቶች ይኖሩታል፣

፪/ የመርማሪ ቦርዱ አባላት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሰየማሉ::

**፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ጀምሮ ለስድስት ወራት የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "Constitution and Constitutional order Defence from Threat State of Emergency Proclamation No.2/2018 Approval Proclamation No. 1083/2018."

**2. <u>Ratification of the State of Emergency Proclamtion</u>**

The Constitution and Constitutional order Defence from Threat State of Emergency Proclamation declared by the Council of Ministers on the 16th day of February, 2018 is hereby ratified.

**3. <u>State of Emergency Inquiry Board</u>**

1/ The State of Emergency Inquiry Board indicated under the Constitution and Constitutional order Defence From Threat State of Emergency Proclamation No.2/2018 is established under this proclamation. It shall have the power and duties indicated under Article 8 and Article 9 of the Constitution and Constitutional Order Defence From Threat State of Emergency Proclamation No.2/2018 and Article 93 (5) and (6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

2/ Members of the Inquiry Board shall be assigned by the House of Peoples' Representatives.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force as of the 16th day of February 2018 for six months.

**Done at Addis Ababa, this 23rd day of March, 2018.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**